በአማራ ብሔራዊክልላዊመንግሥት
ፍትሕ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር፡- የሕ/ምክ/ማር/ማጠ/1027/18

ቀን 24/04/2018 ዓ/ም

ለመንገድ ትራንስፖርት ሎጅስቲክ ቢሮ
ባህርዳር፤

**ጉዳዩ፡ መመሪያም ዝገባን ይመለከታል**

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም እንደተደነገገው ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው በመላክ እንዲሁም አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አዋጁ በወጣ በ1 (አንድ) ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮው በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል።

በዚህ መሰረት የመንገድ፣ ትራንስፖርትና ሎጅስቲክ ቢሮ በቁጥር ት/ሎ/ባ/03-360/18 በቀን 24/03/2018 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር የአደረጃጀትና አሰራር መመሪያ ቁጥር 11/2011 ዓ.ም ምዝገባ እንዲከናወን መላኩ ይታወሳል።

ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 1 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተላከለትን መመሪያ ቁጥር 11/2011 ዓ.ም ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮና አስተካክሎ መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 29/2018 ዓ.ም ሆኖ ስራ ላይ እንዲውል የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ......ገጽ በዚህ ሽኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

ሙሉጎጃም እንየዉ
በሕግ ምክር፣ ማርቀቅና
ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት
የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ//

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፣ (ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት

ፍትሕቢሮ

Tel.No 058 222 0794/793
☎ 058 220 37 57
✉ 995
Fax- 0582221530

# በአብከመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ
# የተሻሻለ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር የአደረጃጀትና አሰራር መመሪያ

ታህሳስ/2018 ዓ.ም

ባህር ዳር

# መመሪያ ቁጥር 29/2018

# በአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ የተሻሻለ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር የአደረጃጀትና አሰራር መመሪያ

መንግስትበትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ላይ የተሰማሩ የተሽከርካሪ ባልንብረቶች በግል ከማስራት ይልቅ በማህበር ተደራጅቶ መስራታቸዉ ለባለሃቱ፣ ለህዝቡ እና ለመንግስትየሚሰጠዉ ጥቅም ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብበማህበር ተደራጅተዉ ስምሪት እንዲሰጡ በአዋጅ ቁጥር 468/97 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 2 የፈቀደ በመሆኑ፤

በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀዉን የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት የአደረጃጀትና የአገልግሎት አሰጣጥ የአሰራር መመሪያ መነሻ በማድረግየክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ መመሪያ በማዘጋጀት በመመሪያዉ መሰረት ከ62 በላይለሚሆኑ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት ፈቃድ በመስጠት ማህበራቱ በክልሉ በተለያዩ ቦታዎች ላይ የትራንስፖርት አገልግሎትበመስጠት ላይየሚገኙ ስለሆነ፤

በወቅቱ የተዘጋጀዉ መመሪያ በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ በመምጣት ላይ ያለዉንየህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ታሳቢ ያለደረገ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በአፈጻጸም ላይችግር እያጋጠመ በመሆኑ፤

በመሆኑም የወቅቱን የትራንስፖርት እንቅስቃሴ ግምት ዉስጥ ያስገባ አዲስ መመሪያ ማዘጋጀት የግድ ሆኖ በመገኘቱ አሁን እየተሰራበት ያለዉንመመሪያዉን ሙሉ በሙሉ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ በተሻሻለው የአብክመ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ማዳራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 264/2011 አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 1(ሰ) ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የተሸሻለው የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር የአደረጃጀትና አሰራር መመሪያ ቁጥር 29/2018 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ

1/ **"ቢሮ"** ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት መንገድና ትራንስፖርት ቢሮነዉ፤

2/ **"ጽህፈት ቤት"** ማለት በክልሉ የሚገኙ የወረዳ መንገድና ትራንስፖርት ጽህፈት ቤቶች ነዉ ፤

3/ **"ኦፕሬተር"** ማለት የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠትተመዝግቦ የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠዉ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረት ነው፤

4/ **"ማህበር"** ማለት ከአሁን ቀደም በወጣዉ መመሪያ መሰረት የተቋቋሙና በዚህ መመሪያ መሰረት ወደፊት የሚቋቁሙ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር ነው፤

5/ **"የማህበር ፈቃድ"** ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት መስፈርቱን ለሚያሟሉለህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበርየሚሰጥ ፈቃድ ነዉ፤

6/ **"የማህበር ፈቃድ እድሳት"** ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት መስፈርቱን ለሚያሟሉ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት በአመት አንድ ጊዜ የሚደረግ የማህበር ፈቃድ እድሳት ነው፤

7/ **"ልዩ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር"** ማለት በመደበኛ ሥምሪት መሥመሮችም ሆነ በሌሎች በተጓዡና በአገልግሎት ሰጪው መካከል በሚደረግ ስምምነት መሰረት የትራንስፖርትአገልግሎት እንዲሰጡ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጣቸዉ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች የሚያቋቁሙት ማህበር ነዉ፤

8/ **"መደበኛ ደረጃ አንድ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር"** ማለትኦፕሬተሮች ባቀረቡት መርሐ ግብር መሠረት በሚሠማሩበት የሥምሪት መሥመርበተመጣጣኝ ታሪፍና የአገልግሎት ጥራት ለኅብረተሰቡ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ተሽከርካሪዎች በመሥፈርቱ መሠረት ተመዝነው ከ80-100 ነጥብ ያገኙ እና ደረጃ አንድ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጣቸዉ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች የሚያቋሙት ማህበርነዉ፤

9/ **"መደበኛ ደረጃ ሁለት የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር"** ማለት ኦፕሬተሮች በቀረቡት መርሐ ግብር መሠረት በሚሠማሩበት የሥምሪት መሥመር በተመጣጣኝ ታሪፍና የአገልግሎት ጥራት ለኅብረተሰቡ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ተሽከርካሪዎች በመሥፈርቱ መሠረት ተመዝነው ከ65-79.99 ነጥብ ያገኙ እና ደረጃ ሁለት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጣቸዉ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች የሚያቋሙት ማህበር ነዉ፣

10/ **"መደበኛ ደረጃ ሶስት የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር"** ማለት ኦፕሬተሮች በቀረቡት መርሐ ግብር መሠረት በሚሠማሩበት የሥምሪት መሥመር በተመጣጣኝ ታሪፍና የአገልግሎት ጥራት ለኅብረተሰቡ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ተሽከርካሪዎች በመሥፈርቱ መሠረት ተመዝነውከ50-64.99 ነጥብ ያገኙ እና ደረጃ ሶስት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጣቸዉ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች የሚያቋሙት ማህበር ማለት ነዉ፤

11/ **"ድርጅት"** ማለት የህዝብ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት በንግድ ህጉ መሰረት የተቋቋሙና ህጋዊ እውቅና የተሰጠዉ የትራንስፖርትድርጅት ማለት ነዉ፤

12/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

13/ በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በክልላችን የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ ፈቃድ በተሰጣቸዉ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት፣የማህበራት አባላት እና የማህበራት አመራሮችና ቅጥር ሰራተኞች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት ፈቃድ አይነቶች እና ፈቃዱን ለመዉሰድ መሟላት ያለባቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች

## 4. የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት ፈቃድ አይነቶች

ቢሮዉ አራት አይነትየህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች የማህበር ፈቃድ ይሰጣል፡፡ የሚሰጡ የማህበር ፈቃድ አይነቶች፡-

1/ ልዩ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር ፈቃድ

2/ መደበኛ ደረጃአንድ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር ፈቃድ

3/ መደበኛ ደረጃሁለት የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር ፈቃድ

4/መደበኛ ደረጃሶስት የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር ፈቃድ

## 5. ፈቃዱን ለመዉሰድ መሟላት ያለባቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች

1/ በህዝብ ትራንስፖርት ማህበር ለመደራጀት ጥያቄ የሚያቀርቡ ኦፕሬተሮች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መስፈርቶቹም፡-

ሀ) ተሽከርካሪው የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት በክልሉ የተመዘገበ እና የወቅቱን አመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ያለፈ፤

ለ) አዲስ /የታደሰ/ የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፤

ሐ) ጊዜዉ ያላለፈበት የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ፡፡

2/ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች የማህበር ፈቃድ የሚሰጠዉ ተመሳሳይ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ/ ደረጃ/ ያላቸዉ ኦፕሬተሮች ጥያቄ ሲያቀርቡ ነዉ፤

3/ ከላይ በአንቀጽ 5(2) የተገለጸዉ ቢኖርም የተለያየ የመጫን አቅም ያላቸው የተሽከርካሪ ባለንብረቶች በአንድ ማህበር መደራጀት ይችላሉ፤

4/ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበር ለማቋቋም ጥያቄ የሚያቀርቡ ኦፕሬተሮች የመስራች አባላት ዝቅተኛዉ ቁጥር ለመደበኛ ደረጃ አንድ፣ለመደበኛ ደረጃ ሁለት እናለመደበኛ ደረጃሶስት50 ተሽከርካሪ ሲሆን ጣሪያዉ/መጨረሻዉ/ 350 ተሽከርካሪ ይሆናል፤የልዩ የመስራች አባላት ዝቅተኛዉ ቁጥር 15 ተሽከርካሪ ሲሆን ጣሪያዉ/መጨረሻዉ/ 100ተሽከርካሪ ይሆናል፡፡

5/ ከላይ በአንቀጽ 5(4)የተገለጸዉ ቢኖርም ቢሮዉእንደ ሁኔታዉ እያየ በጥናት የመስራች አባላት ቁጥር እና ጣሪያዉን ሊያሻሽለዉ ይችላል፤

6/ ለማህበሩ ፈቃድ የሚሰጠዉ ቢሮዉ ወይም በተዋረድ ያሉ መምሪያዎች በተገኙበት የጠቅላላ ጉባኤ ተካሄዶ የመመስረቻ ጹሁፍ እና ከሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር የአደረጃጀትና አሰራር መመሪያ ቁጥር11/2011 ባልተቃረነ ሁኔቴ የተዘጋጀ የዉስጥ መተዳደሪያ ደንብ ጸድቆ የቦርድ አባላትና የኦዲትና እንስፔክሽን ከተመረጠ በኋላ ነዉ፤

7/ ከላይ በአንቀጽ 5(6) የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የነባር ማህበራት የዉስጥ መተዳደሪያ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ የዉስጥ መተዳደሪያ ደንባቸዉን እንዲያሻሽሉ መደረግ ያለበት ሲሆን መተዳደሪያ ደንባቸዉን የማያሻሽሉ ማህበራት ፈቃዳቸዉ መታደስ የለበትም፤

8/ የትራንስፖርት ማህበራት አዲስ ፈቃድ ሲወስዱ ለቢሮዉወይም በተዋረድ ላሉ መምሪያዎች የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላሉ፡፡የአገልግሎት ክፍያዉ በአባላት ቁጥር የተወሰነ ሲሆን የሚከፍሉት ክፍያ፡-

ሀ) የአባላት ብዛት 50 ከሆነ ብር 250

ለ) የአባላት ብዛት ከ51- 100 ከሆነ ብር 500

ሐ) የአባላት ብዛት ከ101 በላይ ከሆነ ብር 1000 ይሆናል

9/ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበር ለመመስረት ጥያቄ የሚያቀርቡ ኦፕሬተሮች ከዚህ በታች የተገለጸዉን የሰው ሃይል እና የቢሮ አደረጃጀት ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሀ) የሰው ሃይል አደረጃጀት

በማህበሩ ዋና ጽ/ቤት መሟላት ያለበትየሰዉ ሃይል በተመለከተ፡-

1) ሥራ አስኪያጅ ------------------------------------------------------------ብዛት1/አንድ/፤

2) የኦፕሬሽን/የስምሪት ባለሙያ/ ለዋናዉ ጽ/ቤት --------------------------ብዛት1/አንድ፤

3) የኦፐሬሽን/የስምሪትባለሙያ/ለቅ/ጽ/ቤት/ለስምሪት ጣቢያ/ ------------------- ብዛት ቢያንስ 1/አንድ፤

4) የመረጃና የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ፈጠራ ባለሙያ--------------------------ብዛት 1/አንድ/

5) የሂሳብ ባለሙያ------------------------------------------------------------------ብዛት 1 /አንድ/፤

6) ሌሎች የስራ መደቦች በማህበሩ የሚወሰን ይሆናል፤

7) ማህበሩ ተቀጣሪ ሰራተኞች ከዚህ በታች የተገለጸዉን የትምህርት ዝግጅት ማሟላት አለባቸዉ፡፡ ይህዉም፡-

ሀ) ስራአስኪያጅ የመጀመሪያ ድግሪ እና ከዚያ በላይ በማኔጅመንት፣ በቢዝናስ አድሚኒስትሬሽን፣ በህዝብ አስተዳደር፣በኢኮኖሚክስ፣ በህግ፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣በትራንስፖርት ማኔጅመንትእና በተገለጹት የትምህርት ዝግጅቶች አቻ/ተመሳሳይየትምህርት ዝግጅት ያለዉናከስራ መደቡ ጋር አግባብነት ያለዉ ቢያንስ ሁለት አመት የስራ ልምድ፤

ለ) የኦፐሬሽን /የስምሪት ባለሙያ/ ለዋናዉ ጽ/ቤትና ለቅ/ ጽ/ቤትዲፕሎማ እና ከዚያ በላይ በማኔጅመንት፣ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን፣ በህዝብ አስተዳደር፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሕግ፣ በስታስቲክስ፣ በኮምፒዉተር ሳይንስ፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣ ማኔጅመንት፣ ኢንጂነሪንግ፣ በመካኒካል ኢንጂነሪንግ፣ በአውቶሞቲቭ እና ከላይ በተገለጹት የትምህርት ዝግጅቶች አቻ/ተመሳሳይ፤

ሐ) የመረጃና የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ፈጠራ ባለሙያ ዲፕሎማና ከዚያ በላይ በማኔጅመንት፣ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን ፣በህዝብ አስተዳደር፣ በኢኮኖሚክስ፣በስታቲስቲክስ፣በኮምፒዉተርሳይንስ፣በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣ ማኔጅመንት፣ኢንጂነሪንግ፣በመካኒካል ኢንጂነሪንግ፣ በአውቶሞቲቭ በስታስቲክስ፣ በማቲማቲክስ፣ ኢንፎርሜሽን ሳይንስ፣ በኮምኒኬሽን፣ በህግ፣ በአዉቶመካኒክ፣ በአዉቶሞቲቭእና በተገለጹት የትምህርት ዝግጅቶች አቻ/ተመሳሳይ፤

መ) የሂሳብባለሙያዲፕሎማና ከዚያ በላይ በአካዉንቲንግ፣ በፋይናንስ፣ በማኔጅመንት፣ እና በተገለጹት የትምህርት ዝግጅቶች አቻ/ተመሳሳይ የትምህርት ዝግጅት ያለዉ፤

8) የሴቶችን ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አኳያ ማህበሩ ከሚቀጥራቸዉ ሰራተኞች መካከልቢያንስ አንድ ሴት መሆን አለበት፡፡

ለ) የቢሮ አደረጃጀትና የመገልገያ መሳሪያዎች

1) የስራ አስኪያጅ ቢሮ፤ ስፋቱ ቢያንስ 3ሜትር በ3 ሜትር የሆነና ደረጃዉን የጠበቀ ወንበርና ጠረንቤዛ እንዲሁም እንግዶች የሚያርፉበት ቢያንስ 4 ወንበር የተሟላለት፤
2) የሰራተኞች ቢሮ፤ ለእያንዳንዱ ሰራተኛ ስፋቱ ቢያንስ 2ሜትር በ3 ሜትር የሆነ ቢሮ ወይንም ሁሉንም ሰራተኛ ማለትም የኦፕሬሽን /የስምሪት/፣ የመረጃና የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ፈጠራ እና የሂሳብ ባለሙያ ሊይዝ የሚችል ሰፊ ቢሮ ያለዉ ሆኖ በእያንዳንዱ ሰራተኛ ልክ ወንበርና ጠረንቤዛ የተሟላለት መሆን አለበት፤
3) መደበኛስልክ እና ፋክስ፤
4) ቢያንስ አንድ ኮምፒውተር እስከ ፕሪንተሩ፤
5) ሰነዶች የሚቀመጡበትቢያንስአንድ የፋይል ካብኔት ወይም መደርደሪያ ሽልፍ፡፡

## ክፍል ሶስት

## የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት ፍቃድ እድሳት

### 6. የፍቃድ እድሳት የሚደረግባቸው ሁኔታውች

1/ የማህበሩ ፈቃድ የሚታደሰዉ የማህበሩ ፈቃድ የተሰጠበት ጊዜ በተጠናቀቀ በመጀመሪያዉ ወር ያለ ቅጣት ፈቃዱ ይታደስለታል፡፡ የማህበሩ ፈቃድ የተሰጠበት ጊዜ በተጠናቀቀ በሁለተኛዉ እና በሶስተኛዉወር የሚመጣ ማህበር ተቀጥቶ ይታደስለታል፡፡ ከዚህ ጊዜ ዉጪ የሚመጣ ማህበር ፈቃዱ አይታደስለትም/ ፈቃዱ ይሰረዛል/ ፤

2/ ከላይ በአንቀጽ 6(1)በተገለጸዉ መሰረትየማህበሩ ፈቃድ የሚታደሰዉ የሰዉ ሃይል፣ የቢሮ አደረጃጀት ፣የአባላት መረጃ መሟላቱ ሲረጋገጥናየማህበሩ የፋይናንስ

አጠቃላይ እንቅስቃሴ ህጋዊ በሆነ የዉጪ ኦዲተር ተመርምሮና በአባለቱ ጸድቆ በቢሮዉ ተቀባይነት ሲገኝ ነዉ፤

3/ በአንቀጽ 6(2) የተገለጸዉ ቢኖርም የማህበር አባልነት ለመሆን መስፈርቱን ያላሟሉ የተሸከርካሪ ባለንብረቶች በሚኖሩበት ወቅት ከማህበሩ እንዲሰረዙ ተደርጎ መስፈርቱን ባሟሉ የተሸከርካሪ ባለንብረቶች ቁጥር ልክ ፈቃዱ ይታደሳል፤ በእድሳት ወቅት መስፈርቱን ያሟሉ የተሸከርካሪ ባለንብረቶች ቁጥር ከ50 በታች ከሆነ ማህበሩ እንደ ማህበር ለመቀጠል የሚያስችል ቁመና መኖሩን ማረጋገጥ ከተቻለ /የሰዉ ሃይል፣ ቢሮ እና የቢሮ መገልገያ መሳሪያዎችን የሚያሟል ከሆነ/ የማህበሩ ፈቃድ ይታደስለታል፤ ማህበሩ እንደ ማህበር ለመቀጠል የማያስችል ቁመና የሚኖረዉ ከሆነ የማህበሩ ፈቃድ ይሰረዛል፤

4/ ከላይ በአንቀጽ 6(1)በተገለጸዉ መሰረት ማኅበሩ ለእያንዳንዱ ላለፈበት ወር ብር 300 /ሶስት መቶ ብር/ ተቀጥቶ ፈቃዱ ይታደስለታል፤

5/ የትራንስፖርት ማህበራትፈቃድ እንዲታደስላቸዉ ጥያቄ ሲያቀርቡለቢሮዉ የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላሉ፡፡ የአገልግሎት ክፍያ መጠን በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ8 ከፊደል ሀ እስከ ሐ በተገጸዉመሰረት ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## የትራንስፖርት ማህበራት አባላት መብትና ግዴታዎች፤

### 7. የአባላት መብቶች

1/ በማህበሩ ዉስጥ የመምረጥም ሆነ የመመረጥ፤

2/ ማህበሩ ለአባላቱ በሚሰጠዉ ማንኛዉም አገልግሎት እኩል የመጠቀም፤

3/ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ፡ ማህበሩ የሚመራባቸዉን መመሪያዎችና አደራጁ አካል በየጊዜዉ የሚያወጣቸዉን መመሪያዎች የማግኘት፤

4/ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች ላይ መገኘት፣ ለማህበሩ የተሻለ የስራ እንቅስቃሴ መፈጠር የሚረዱ አስተያየቶችና የዉሳኔ ድምጽ የመስጠት መብት ይኖረዋል፡፡ በዚህም መሰረት አንድ አባል አንድ ድምጽ ይኖረዋል፤

5/ በማህበሩ መደበኛና አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች ላይ ተገኝቶ ተሳትፎ ማድረግ፤

6/ በመንግስትም ሆነ በማህበሩ የስራ አመራር ቦርድ መስተካከል አለባቸዉ የሚላቸዉን ችግሮች እንዲስተካከሉ የመጠየቅ፣ ካልተፈጸመም ለአደራጁ አካል ማሳወቅ

8. <u>የአባላትግዴታዎች</u>

1/ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የስልጣን ዉክልና በተሰጠዉ የሰራ አመራር ቦርድ የሚተላለፉ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን መፈጸም፣

2/ በመንግስት የሚወጡ ህጎች ደንብና መመሪያዎችን አክብሮ በስራ ላይ ማዋል፣

3/ በአባልነት ያስመዘገበዉን ተሽከርካሪ በስምሪት ላይ ማቅረብ፣

4/ አገልግሎት በሚሰጥበት ተሽከርካሪ ላይ የቴክኒክ ችግር ሲገጥመዉ ለማህበሩ ማሳወቅ፣

5/ በጠቅላላ ጉባኤ የሚወሰኑልዩ ልዮ ክፍያዎች መክፈል፡፡

## ክፍል አምስት

## ከማህበር አባልነት መልቀቅ፣ ዝዉዉርና ስረዛ እና የትራንስፖርት ማህበራት ስለ መፍረስ

9. <u>ከማህበር አባልነት ስለመልቀቅ</u>

1/ ማንኛውም የማህበር አባል ከማህበሩ በራሱ ፈቃድ ለመልቀቅ የጽሁፍ ማመልከቻ ሲያቀርብና ከማህበሩ በሰነድ የወሰደውን ንብረት በሰነድ ወይም በአይነት ወይም በገንዘብ ካስረከበ ማህበሩን ሊለቅ ይችላል፣

2/ መለቀቂያ እንዲሰጠዉ በጽሁፍ ያቀረበ አባል የሚጠበቅበትን ግዴታ እስከተወጣ ድረስ እጅግ ቢዘገይ እስከ አምስት ቀናት ዉስጥመልቀቂያ ሊሰጠዉ ይገባል፣

3/ ከላይ በአንቀጽ 7.1.2 የተገለጸዉ ቢኖርም መልቀቂያ የተሰጠዉ ኦፕሬተር የጸደቀለት የስራ መርሃ ግብር እስከሚጠናቀቅ ድረስ በተመደበበት የስምሪት መስመር መስራት አለበት፣

4/ በመልቂቂያ አሰጣጥ ሂደት በአባሉና በማህበሩ መካከል መግባባት ካልተቻለ በሚቀርበዉ ጥያቄ መሰረት ለማህበሩ ፈቃድ የሰጠዉ ቢሮ/ መምሪያ/ጣልቃ በመግባት ችግሩ እንዲፈታ ያደርጋል፣

5/ መልቀቂያ የተሰጠዉ ኦፕሬተር በክልሉ ዉስጥ በተቋቋመ ሌላ ማህበር ለመደራጀት ፍላጎት ካለዉ ቀድሞ ከነበረበት ማህበር የተሰጠዉን መልቀቂያ በማቅረብ መደራጀት ይችላል፣

6/ መልቀቂያ የተሰጠዉ/የተሽከርካሪ ባለንብረት ወደ ነበረበት ማህበር ለመመለስ ከፈለገ ጥያቄዉን ለስራ አስኪያጁበማቅረብ ተቀባይነት ካገኘ መመለስ ይችላል፡፡

## 10. ከማህበር ዝዉዉር ስለማድረግ

የማህበር አባላትን ከአንድ ማህበር ወደ ሌላ ማህበር ለመዛወር የሚያበቁ ምክንያቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

1/ በሽያጭ ምክንያት ሊብሬው በገዢው ስም ሲዛወር እና ገዥው ወደ ሌላ ማህበር ለመዛወር ጥያቄ ሲያቀርብ፤

2/ እንደ ማህበር አባልነት እኩል አገልግሎት ባለማግኘቱና ሌሎች ተያያዥ ችግሮችና አለመግባባቶች በባለንብረት እና በማህበሩ መካከል ሲከሰት እና በአደራጁ አካል ሲረጋገጥ፤

3/ የማህበሩ ተሽከርካሪ ቁጥር ከተደራጀበት መስፈርት በታች በመሆኑ እንዲሁም ማህበሩ በተለያየ ምክንያት ሲፈርስ የአባላት ዝውውር በቢሮዉ ሲፈቀድ፡፡

## 11. ከማህበር አባልነት ስለመሰረዝ

1/ አባሉ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብመሰረት ከማህበሩ አባልነት ሊያሰርዘዉ የሚያስችሉ ተጨባጭ ጥፋቶች አጥፍቶ ሲገኝ እና እገዳዉ በጠቅላላ ጉባኤውሳኔ ሲሰጠው፤

2/ በጠቅላላ ጉባኤዉ የተወሰነዉን ክፍያዎች ለመክፈል ፍቃደኛ ሳይሆን ሲቀር፤

3/ አባሉ በራሱ ጊዜ ማህበሩን መልቀቅ ከፈለገ፤

4/ የማህበር አባላት ቁጥር ከመነሻ አባላት ቁጥር በታች ሆኖ ሲገኝ፤

5/ ከላይበአንቀጽ 11(4) የተገለጸዉ ቢኖርምየፈረሰዉ ማህበር አባላት በሙሉ ወደ ሌላ ማህበር መዛወር ከፈለጉ በማህበሩ ያለዉን ሃብትና ንብረት ይዞ መዛወር ይችላል፤

6/ አባሉ በሞት ሲለይ፤

7/ ከላይ በአንቀጽ 11(6) የተገለጸዉ ቢኖርም ወራሽ ካለ እና ህጋዊ የዉርስ ማስረጃ ከሚመለከተዉ ተቋም ማምጣት ከቻለ ወራሹ የምዝገባ ክፍያ ሳይከፍል የማህበሩ አባል ሆኖ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

## 12. የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት ስለመፍረስ

1/ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት ከዚህ በታች በተሰረዘሩት ምክንያቶች ሊፈርስ ይችላል፤

ሀ) የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤው 3/4ኛ የአባልነት ድምጽ ብልጫ ማህበሩ እንዲፈርስ ሲወስኑ እና ዉሳኔዉለክልሉመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ/ ቀርቦ ሲፀድቅ፤

ለ) በዚህ መመሪያ ማህበሩን ሊያሰረዝ የሚያስችል ጥፋት ተፈጽሞ ሲገኝ ወይም አደራጁ አካል መፍረስ ይገባዋል ብሎ ሲወስን፤

ሐ) ማህበሩ እንዲፈርስ በፍርድ ቤት ውሳኔ ሲሰጠዉ፤

መ) የማህበርአባላት ቁጥር ከመነሻ ቁጥር በታች ሲሆን።

2/ ከላይ በአንቀጽ 12(1)ከፊደል ሀ-ሐበተጠቀሱት ምክንያቶች ማህበሩ ከፈረሰ የማህበሩ ገንዘብና ንብረት በፍትህ ብሔር ህግ ቁጥር 467 በተደነገገው መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

3/ በአንቀጽ 12(1)በፊደል መ ምክንያት የፈረሰ ማህበር አባሉ በሙሉ ወደ ሌላ ማህበር መዛወር ከፈለግ ያለዉን ሃብትና ንብረት ይዞ መዛወር ይችላል።

## ክፍል ስድስት

## ስለ ህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት አስተዳደርና አመራር

### 13. የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት የዉስጥ ገቢ

1/ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት የፋይናንስ ምንጭ ከሚከተሉት አንዱ ወይም ሁሉም ሊሆን ይችላላ፡፡ይህዉምየማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ከሚወስነዉ

ሀ) የአገልግሎት ክፍያ/ኮሚሽን፤

ለ) ከአባላት ቅጣት

ሐ) አባላት ከሚደርጉት ልዩ ልዩ መዋጮ፤

መ) አባላትከሚከፍሉት የመመዝገቢያ ክፍያ ሆኖ ከፍተኛዉ የመመዝገቢያ ክፍያ ከብር 1500 መብለጥ የለበትም፤

2/ የማህበሩ የውስጥ ገቢ ማህበሩ የተቋቋመበትን ተግባርና ሃላፊነት ለማሳካት ለሚረዱ ጉዳዮች ብቻ ማዋል ይገባዋል፤

3/ ማህበሩ የበጀት አመቱ በተጠናቀቀ ከአንድ እስከ ሁለት ወር ባለዉ ጊዜ የማህበሩ ሂሳብ እንቅስቃሴ ህጋዊነት ባለዉ የውጪ ኦዲተር መመርመርአለበት፤

4/ የማህበሩ ሂሳብ እንቅስቃሴ በውጭ ኦዲተር ተመርምሮ ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ካልጸደቀ የማህበሩ ፈቃድ አይታደስም፡፡

## ክፍል ሰባት

## በየደረጃዉ ያሉ አደረጃጀቶች ተግባርና ሃላፊነቶች

### 14. የቢሮዉ ተግባርና ሃላፊነት

1/ ማህበር ለመመስረት ጥያቄ የሚያቀርቡ ኦፕሬተሮች ያዘጋጁቱን የመመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ መርምሮ በማጽደቅ ፈቃድ መስጠት፤

2/ የትራንስፖርት ማህበራቱ በወሰዱት ፈቃድ መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን መከታተል መቆጣጠር፡፡መመሪያዉንአክብረዉ በማይሰሩ የማህበራቱ አባላት፣ የቅጥር ሰራተኞች እና የቦርድ አመራሮች ላይ እንደአስፈላጊነቱ የዲሲፒሊን እርምጃ መውሰድእና እንዲወሰድባቸዉ ማድረግ፤

3/ የማህበሩ አባላት አደረጃጀታቸውና አሰራራቸው ወደ ዘመናዊየንግድ ኩባንያ እንዲሸጋገሩ የአቅም ግንባታ እና የድጋፍ አገልግሎትይሰጣል፤

4/ የወጣዉን መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ማሻሻል፡፡

### 15. የመምሪያዎች ተግባርና ሃላፊነት

1/ ማህበር ለመመስረት ጥያቄ የሚያቀርቡ ኦፕሬተሮች ያዘጋጁቱን የመመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ መርምሮ በማጽደቅ ፈቃድ መስጠት፤

2/ ኦፕሬተሮች በሚያቀርቡለት መርሃ ግብር መነሻ ማህበሩ የሚያቀርበዉን መርሃ ግብር መርምሮ ማጽደቅና ስምሪቱን በበላይነት ማስፈጸም፤

3/ ከላይበአንቀጽ 15(2) የተጠቀሰዉ ቢኖርም ማህበሩ ያቀረበዉ መርሃ ግብር ትክክል ካልሆነ ቢሮዉየኦፕሬተሩን መርሃ ግብር ተቀብሎ በማጽደቅ ስምሪት እንዲሰጥ ያደርጋል፤

4/ ማህበሩ ሁሉንም የስምሪት መስመሮች ያካተተ የስራ መርሃ ግብር መቅረቡን ያረጋግጣል በስራ መርሃ ግብሩ ያልተካተቱ መስመሮች በሚኖርበት ወቅት እንዲካተቱ ያደርጋል፤

5/ የትራንስፖርት ማህበራቱ በወሰዱት ፈቃድ መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን መከታተል መቆጣጠር፡፡መመሪያዉንአክብረዉ በማይሰሩ የማህበራቱ አባላት፣ የቅጥር ሰራተኞች እና የቦርድ አመራሮች ላይ እንደ አስፈላጊነቱ የዲሲፒሊን እርምጃ መውሰድእና እንዲወሰድባቸዉ ማድረግ፤

6/ የማህበሩ አባላት አደረጃጀታቸውና አሰራራቸው ወደ ዘመናዊየንግድ ኩባንያ እንዲሸጋገሩ የአቅም ግንባታ እና የድጋፍ አገልግሎትይሰጣል፡፡

## 16. የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት ተግባርና ሃላፊነቶች

1/ በማህበር አባላትነት ለመመዝገብ የሚፈልጉ እና መመዘኛውን የሚያሟሉ ኦፕሬተሮች የዘር የሃይማኖት የጾታ እና የፖለቲካ ልዩነት ሳይደረግባቸው በአባልነት መመዝገብ፤

2/ የማህበሩ አባላት ባወጡት መርሃ ግብርመሰረት ያደረግ መርሃግብር አጣጥሞ በማዘጋጀት እና የኦፕሬተሩን መርሃ ግብር ኮፒ በማያያዝ ለቢሮዉ ማቅረብ ሲፈቀድለት ስምሪቱን ማስፈጸም፤

3/ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በሚፈጠሩበት ወቅት እና ለልዩ ስራ የማህበሩ አባላት ተሽከርካሪዎች ለስምሪት ሲፈለጉ በሚሰጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥማቅረብ፤

4/ የማህበሩ እዉቅና በተሰጠዉ በአንድ ወርጊዜ ዉስጥ በማህበሩ ስም የባንክ አካውንት ከፍቶ በተከፈተዉ አካዉንት ገንዘብ ገቢ ማድረግ፤

5/ የማህበሩ እዉቅና በተሰጠዉ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ተቀጣሪ ሰራተኖች እና የቢሮ አደረጃጀት፣የመንገደኞች ትኬት፣ደረሰኝ፣ የእቃ ታግ፤የራስጌና የግርጌ ማህተም፤የማህበሩን ደረጃና አርማ የያዘ ስቲከር/ሎጎ/ ማሳተም፤

6/ የማህበሩ እዉቅና በተሰጠዉ ስድስት ወር ዉስጥ አገልግሎት በሚሰጥበት መናኀሪያ፣ የምድር የእቃ መመዘኛ ሚዛን ማቅረብ አለበት፤

7/ የማህበሩ አባላት ተሽከርካሪዎች በጉዞ ላይ እያሉ ሲበላሹ ትክ ማቅረብ የግድ በሚሆንበት ወቅት ትክ ማቅረብ፤

8/ ቢሮው ስራ ላይ እንዲውሉ የሚያስተላልፈውን ታሪፍ የማህበሩ አባላት በወቅቱ እንዲደርሳቸው ማድረግ እና ስራ ላይ መዋሉን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፤

9/ የማህበሩ አባላት በሆኑ ተሽከርካሪዎች ውስጥ ለሚሰሩ ሰራተኞች ሰራተኝነታቸውን ሊያረጋግጥ የሚችል በፎቶ ግራፍ በተደገፈ መታወቂያ እና የደንብ ልብስ እንዲያዘጋጁ ማድረግ፤

10/ የአባላቱ ተሽከርካሪዎች እና አሽከርካሪዎች የሚያደርሱትን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ የሚያስችል የግንዛቤ ማዳበሪያ ስልጠና ማመቻቸትና አደጋን በመከላከል እንዲያገለግሉ ማድረግ፤

11/ ስለመንገድ ትራንስፖርት የወጡትን ህጐች ፣ደንቦችና መመሪያዎች አባላት እንዲያውቁና አክብረው እንዲያስተገብሩ ማድረግ፤

12/ የማህበሩን አባላት የስራ አቅም በማጐልበትና የሙያ ብቃት በማሳደግ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ መሻሻል እንዲታይ በየጊዜው ጥናቶችን ማስጠናት 13/ በአገልግሎት አሰጣጥም የአሽከርካሪዎችና አግልጋሎት ሰጭ ሰራተኞች የስነ ምግባር ሁኔታ የተሟላ መሆኑን ማረጋገጥ፤

14/ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና ሰነዶችን በሚገባ መያዝና በቢሮዉ ሲጠየቅም ማቅረብ፤

15/ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ላይ ባጸደቀው መሰረት ከአባላት ኮሚሽን መሰብሰብ፤

16/ የማህበሩ አባላት ሕግና ደንብን ጠብቀው አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፤

17/ አባላቱን በመወከል የስራ ውሎችን ማካሄድ፡፡

## 17.የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

1/ ለማህበሩ የስራ እንቅስቃሴ ተጠንቶ የቀረበለትን የስራ ዕቅድና ማስፈፀሚያ በጀት መርምሮ ያፀድቃል፤

2/ የማህበሩን የስራ አመራር ቦርድ አባላትን ይመርጣል፣ ይሽራል እንዲሁም ስልጣንና ተግባራቸውን ይወስናል፤

3/ የማህበሩን የውስጥ ኦዲትና ኢንስፔክሽን አባላትን ከአባላቱ መካከል ይመርጣል፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ይወስናል፤

4/ ጉባኤው አምኖባቸው የማህበሩን ሥራ እንዲመሩ ለሚመርጣቸው የሥራ አመራር ቦርድ አባላትና ሌሎች የሥራ አካላት ለሚሰጡት አገልግሎት እንደ አስፈላጊነቱ የሥራ አበል ይወስናል፤

5/ ጉባኤው የስራ አመራር ቦርዱን የስራ ሪፖርት ያዳምጣል፣ በጀት ያሻሽላል፣ ሪፖርት መርምሮ ያፀድቃል፤

6/ ጉባኤው መስፈርቱን በጠበቀና የአሰራር ሥርዓትን በተከተለ መልኩ በሥራ አመራር ቦርዱ ተወዳድሮና ምርጫ ተደርጎ በሚቀርቡለት መሰረት ለበጀት አመቱ የሚሰራ የውጭ ኦዲተር ያፀድቃል፣ የሚቀርብለትንም የሥራ ሪፖርት አዳምጦና መርምሮ ያፀድቃል፤

7/ መስፈርት በጠበቀና የአሰራር ሥርዓትን በተከተለ መልኩተወዳድሮና ተመርጦ ከስራ አመራር በሚቀርብለት መሰረት የማህበሩን ስራ አስኪያጅ ሹመት መርምሮ ያፀድቃል፣ ከሹመትም ያወርዳል፤

8/ ጉባኤው ማህበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ መሰረት በማድረግ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የማህበሩን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፤

9/ በአባላት የሚከፈለውን የአገልግሎት መዋጮና የመመዝገቢያ ክፍያ መጠን ይወስናል፤

10/ ለማህበሩ ዕድገት በስራ አመራር ቦርዱ ተጠንቶ የሚቀርቡለትን የአሰራር ማሻሻያ ጥናቶችን መርምሮ ያፀድቃል፣ ተግባራዊ እንዲሆንም መመሪያ ይሰጣል፤

11/ በማሕበሩ መፍረስ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣ ስለማሕበሩ ንብረትም በፍትሃብሔር ሕጉ መሰረት ተፈፃሚ ያስደርጋል፤

12/ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት የሚፈፅሙትን የስራ ግድፈትና ሕገወጥ ተግባራት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

13/ የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ የሚመሩ አካላትን በየስብሰባው ይመርጣል፣ የሥራ መመሪያም ይሰጣል፡፡

## 18. የጠቅላላ ጉባኤ የአሰራር ስርዓት

1/ የማሕበሩ ጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባውን በአመት 1 ጊዜ ያደርጋል፣ እንደ አስፈላጊነቱም አስቸኳይ ስብሰባ ማድረግ ይችላል፣ የጠቅላላ ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባም በሥራ አመራር ቦርዱ ወይም በውስጥ ኦዲትና ኢንስፔክሽን አካሉ ሊጠራ ይችላል፤

2/ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ተሳታፊ የሚሆኑት የማሕበሩ አባል የሆኑት የተሽከርካሪ ባለንብረቶች ወይም በአባላቱ ልዩ ውክልና የተሰጣቸው ናቸው፤በማሕበሩ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ለሥራ አመራር ቦርድ አባልነት መምረጥ የሚችሉት የተሽከርካሪ ባለንብረቶች ብቻናቸው፤

3/ በማሕበሩ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ለሥራ አመራር ቦርድ አባልነት መመረጥ የሚችሉት የተሽከርካሪ ባለንብረት የሆኑ ብቻ ይሆናሉ፤

4/ የልዩ ውክልና ያላቸው ተሳታፊዎች በሥራ አመራር ቦርድ አባልነት ከመመረጥ እና ከመምረጥ ውጭ ሌሎች መብቶች አላቸው፤

5/ የማሕበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ምልዐተ ጉባኤው ተሟልቷል ሊባል የሚችለው ከጠቅላላ የማህበሩ አባላት 50% በላይ (ከግማሽ በላይ) የሆኑ አባላት መገኘታቸው ሲረጋገጥ ነው፤

6/ ከማህበሩ 1/3ኛ አባላት በጽሁፍ የተደገፈ ጥያቄ ለሥራ አመራር ቦርዱ ካቀረቡ የማሕበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንዲጠራና በቀረበው ጉዳይ ላይ እንዲወያይ ያደርጋል፤

7/ በተጠራው ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ የተገኙ አባላት ምልዐተ ጉባኤ ካልተሟላ ሁለተኛ የስብሰባ ጥሪ በ30 /ሰላሳ/ ቀናት ውስጥ ይደረጋል፡፡ በዚህ የስብሰባ ጥሪ መሰረት በተገኙ አባላት የሚወሰነው ውሳኔም ተፈፃሚ ይሆናል፤

8/ ለቀረበው የአባላቱ ጥያቄ የሥራ አመራር ቦርዱ የማሕበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ለመጥራት ምላሽ ካልሰጠ ወይም የማሕበሩ የውስጥ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ስብሰባውን ለመጥራት ፈቃደኝነት ከሌለው ቢሮው በማህበሩ ወጪ ስብሰባው እንደጠራና ጠቅላላ ጉባኤው በአባላቱ ጥያቄ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

9/ የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በድምጽ ብልጫ ይሆናል፣ የተሰጠው ድምፅ እኩል ሲሆን ስብሰቢው የደገፈው ተፈፃሚ ይሆናል፤

10/ የጠቅላላ ጉባኤው መወያያ አጀንዳ የስራ አመራር ቦርዱ ከስብሰባው 15 ቀናት በፊት አባላት እንዲያውቁት ያደርጋል፣ ከአባላቱ የሚቀርቡ ተጨማሪ አጀንዳ ሲኖሩም በጽ/ቤቱ በኩል ተመዝግቦ እንዲቀርብ ይደረጋል፤

11/ በተያዘው አጀንዳ መሠረት ውይይት ተደርጎ ውሳኔዎች ሲተላለፉ የቃለ ጉባኤ ሰነዱ በስብሰባው ላይ ተሳታፊ የነበሩትን አባላት ሥም ዝርዝርና ስለመገኘታቸው በፊርማ ካረጋገጠበት ኦርጅናል የምዝገባ ሰነድ ጋር ተያይዞ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

## 19. <u>የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ እንዲመራ የሚሰየመው አካል ተግባርና ኃላፊነት</u>

1/ በጉባኤው እንደተመረጠ የራሱን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢና ፀሐፊ መርጦ በጉባኤው ያፀድቃል፣ የስራ ጊዜውም ለተመረጠበት የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ብቻ ይሆናል፤

2/ በዕለቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ሂደት በተያዘው የመወያያ አጀንዳ መሠረት አባላቱ ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በማድረግ ስብሰባውን ይመራል፤

3/ ጠቅላላ ጉባኤ በዚሁ ስብሰባ የማህበሩ ስራ አመራር ቦርድ፣ የውስጥ ኦዲትና ኢንስፔክሽን እንዲሁም በውጭ ኦዲተሮች ስለማሕበሩ ገንዘብና ንብረት አያያዝና

አጠቃቀም ለጉባኤው የሚያቀርቡትን የሥራ ሪፖርት በየደረጃው እንዲያቀርቡ ያደርጋል፡ የቀረቡትን ሪፖርቶች ላይም የጉባኤው አባላት በቂ ውይይት በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያርጋል፤

4/ ጠቅላላ ጉባኤው በስብሰባው ወቅት የቀረቡለትን ጉዳዮች መርምሮ እና ተወያይቶ የሚደርስባቸውን ውሳኔዎች መዝግቦ በተሟላ መረጃ አስደግፎ ስብሰባው እንዳበቃ በሰነድ ተጠቃሎ በጽ/ቤት እንዲያዙ ያደርጋል፤ የስብሰባውን ሂደት የሚገልፅ ቃለ ጉባኤ በሶስት ቀናት ውስጥ ለማህበሩ የስራ አመራር ቦርድና ለቢሮው ትክክለኛ ቅጁ በጽ/ቤቱ በኩል እንዲደርሳቸው ያደርጋል፡፡

## 19. የሥራ አመራር ቦርድ አደረጃጀት

1/ የሥራ አመራር ቦርዱ ከአምስት እስከ ሰባት አባላት ይኖሩታል፤ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሴቶች የቦርድ አመራር ሆነዉ እንዲመረጡ የበኩሉን ድርሻ መወጣት አለበት፤

2/ የቦርድ አመራሮች የትምህርት ዝግጅት 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀና ከዚያ በላይ መሆን አለባቸዉ፤ በምርጫ ወቅት ድግሪና ከዚያ በላይ ያለዉ ቅድሚያ የሚሰጥ ሲሆን ድግሪና ከዚያ በላይ ካልተገኘ ድፕሎማ ፣ ድፕሎማ ካልተገኘ 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀ ሊሆን ይገባል፤

3/ የስራ አመራር ቦርድ የራሱ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢና ፀሐፊ ይኖሩታል፤

4/ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ያለድምፅ የሥራ አመራር ቦርዱ ፀሐፊ ይሆናል፤

5/ የስራ አመራር ቦርድ የስራ ዘመን ለሁለት አመት ይሆናል፤

6/ አንድ አባል በስራ አመራር ቦርድ በተከታታይ ከሁለት ጊዜ በላይ መመረጥ አይችልም፤ ሆኖም ግን ከሁለት አመት ቆይታ በኋላ እንደገና ሊመረጥ ይችላል፤

7/ የሥራ አመራር ቦርዱ እንደአስፈላጊነቱ በንኡሳን ኮሚቴዎች በመዋቀር ሊሰራ ይችላል፤

8/ በአንድ ማህበር የቦርድ አመራርነት አባል ለሁለት ምርጫ ዘመን ያገለገለ አባል አዲስ በሚቋቋም ማህበር ወይም በውህደት በሚቋቋም ማህበር የቦርድ አመራር አባል ሆኖ መስራት የሚችለው ከሁለት ዓመት የጊዜ ቆይታ በኋላ ነው፤

9/ በአንድ ማህበር የቦርድ አመራር አባል ሆኖ ለአንድ ምርጫ ጊዜ ካገለገለ አዲስ በሚቋቋም ማህበር ወይም በውህደት በሚቋቋም ማህበር አንድ የምርጫ ጊዜ ብቻ

የቦርድ አመራር አባል ሆኖ መስራት ይችላሉ፤ የቦርድ አመራር ሆኖ ድጋሚ ለመመረጥ የሁለት አመት የጊዜ ቆይታ መጨረስ ይጠበቅበታል፤

10/ አንድ የተሸከርካሪ ባለንብረት ልዩ እና የተለያየ ደረጃ ተሸከርካሪዉ ቢኖረው እና በተለያዩ ማህበራት አባል ቢሆን በአንድ ጊዜ ከአንድ ማህበር ውጪ በቦርድ አመራርነት ሊመረጥ አይችልም፡፡

## 20. የሥራ አመራር ቦርድ ስልጣንና ተግባር

1/ ለህዝብ ማመላለሻ ባለንብረቶች የተሰጡትን ተግባርና ሃላፊነት በባለቤትነት ይዞ ይመራል ያስተባብራል፤

2/ የሥራ አመራር ቦርዱ የማህበሩን ሥራ አስኪያጅ በስነ-ምግባሩ ምስጉን የሆነ እና የማህበር አባል ያልሆነ አወዳድሮ ይቀጥራል፣ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦም ያፀድቃል፣ ተገቢው የሥራ መዘርዝር ተዘጋጅቶ እንደሰጠው ያደርጋል፤

3/ የሥራ አመራር ቦርዱ በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡትን መመሪያዎችና የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ስራ ላይ ያውላል፤

4/ የማህበሩን የሥራ ዕቅድና ማስፈፀሚያ በጀት ያዘጋጃል፣ በጠቅላላ ጉባኤ ሲፀድቅም ስራ ላይ ያውላል፤

5/ የማህበሩን ሥራ ለማከናወን የሚያስችል ጽህፈት ቤት ያደራጃል፣ እንደአስፈላጊነቱም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይከፍታል፤

6/ የማህበሩን የፋይናንስ እንቅስቃሴ በሕግና ስርዓት እንዲመራ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣ አመራርም ይሰጣል፤

7/ በጠቅላላ ጉባኤው ምርጫ መሰረት የሥራ አመራር ቦርዱ ከቦርዱ በሚወክለው ቦርዱ አባልና የጽ/ቤት ሙያተኛ አማካይነት በማሕበሩ ስም የባንክ ሂሳብ በመክፈት ያንቀሳቅሳል፤

8/ የስራ አመራሩ በሚወስነው የገንዘብ መጠን መሰረት የአመራሩ ቦርድ ሰብሳቢ፣ ስራአስኪያጅ እና የፋይናንስ ክፍል ጣምራ ፊርማ የማህበሩን ገንዘብ ማንቀሳቀስ ይችላሉ፤ ሆኖም ሂሳቡን በወቅቱ ማወራረድ አለበት፤

9/ የስራ አመራሩ በሚወስነው የገንዘብ መጠን መሠረት በስራ አመራሩ ቦርዱ ሰብሳቢ እየተረጋገጠ ሲፈቀድ ብቻ በማህበሩ ስራ አስኪያጅ እና የፋይናንስ ክፍል ጣምራ ፊርማ የማህበሩን ገንዘብ ማንቀሳቀስ ይችላሉ፣ ሆኖም ሂሳቡን በወቅቱ ማወራረድ አለበት፤

10/ የማህበሩ የስራ እንቅስቃሴ የሚገልጽ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፣ በሪፖርት ዝግጅት ሂደት ሥራ አስኪያጅ የሚጠበቅበትን የሥራ ድርሻ መውጣት እንዲችል ተገቢው አመራር ለሥራ አስኪያጅ መስጠት ይኖርበታል፤

11/ የማህበሩን ዓመታዊ ንብረትና ሂሳብ መስፈርት በጠበቀ አሰራር ሕጋዊ ኦዲተር አወዳድሮ በጠቅላላ ጉባኤው አፀድቆ እንደመረመር ያደርጋል፣ የኦዲት ሪፖርቱንም በጠቅላላ ጉባኤው ባፀደቀው በአንድ ወር ውስጥ ለቢሮው ያቀርባል፤

12/ የተጓደሉ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ሲኖሩም የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ በመጥራት በምትክ ምርጫ እንዲሟላ ያደርጋል፤

13/ በዘርፉ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በቢሮው የሚተላለፉ መመሪያዎችን ተቀብሎ ይፈጽማል፣ በአባላቱም እንዲፈፀሙ ያደርጋል ተግባራዊነቱንም ይቆጣጠራል፤

14/ የማህበሩን አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ ይመራል፣ በየደረጃውም ለሚሰጠው አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑትን የሥራ አካላትን በማዋቀርና በሙያተኞችም በማጠናከር እንደሰሩ ያስደርጋል፣ የሥራ አፈፃፀማቸውንም ይቆጣጠራል፤

15/ የማህበሩን ኦፕሬሽናል ስራዎች የሚገልፅ መረጃ ለቢሮው መተላለፉን ያረጋግጣል፣ በአስፈላጊ ወቅት የሚጠየቁ መረጃዎች በወቅቱ እንዲደርሱ ያደርጋል፤

16/ ማህበሩ ለትርፍ የተቋቋመ ባለመሆኑ የማህበራት ንብረትና ገንዘብ ለአባላቱ የጋራ ጥቅም በሚውሉ የተጠኑ ሥራዎች ላይ ከማዋል ባለፈ ከሕግ አግባብ ውጭ ክፍፍል እንዳይፈፀም ያደርጋል፤

17/ ከተመረጠበት የሥራ አመራር ቦርድ አባልነት ውጭ በማህበሩ የሙያዊ አገልግሎት ላይ ወይም በማሕበሩ ሥራ አስኪያጅነት በኃላፊነት ተመድቦ መሥራት አይችልም፡፡

## 21. የሥራ አመራር ቦርድ ሊቀመንበር ተግባርና ኃላፊነት

1/ የቦርዱን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፤

2/ በየደረጃው ያሉትን የማሕበሩን የሥራ አካላት እንቅስቃሴ በበላይነት የሚመራውን የማህበሩን ሥራ አስኪያጅ ይደግፋል፣ ያስተባብራል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይቆጣጠራል፤

3/ በጠቅላላ ጉባኤው የተሰጡ አመራርና የተወሰኑ ውሳኔዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

3/ ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርቶችን የሥራ አመራር ቦርዱን በመወከል ለማሕበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፤

4/ ማህበሩን በመወከል አስፈላጊ ስብሰባዎችን፣ ስልጠናዎችን ይካፈላል፡ ወይም ከቦርዱ አባላት የተወከሉ ክፍሎች እንዲካፈሉ ያደርጋል፤

5/ አስፈላጊ ሲሆን ከመደበኛ ስብሰባ ውጭ የሥራ አመራር ቦርዷን አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል፡፡

## 22.የስራ አመራር ቦርድ ም/ሊቀመንበር ተግባርና ኃላፊነት

1/ ሊቀመንበሩን በቅርብ በመሆን ያግዛል፤

2/ ሊቀመንበሩ ሳይኖር ቦታውን ተክቶ ይሰራል፣

## 23.የስራ አመራር ቦርድ ፀኃፊ ተግባርና ኃላፊነት

1/ የቦርዱን ስብሰባ አጀንዳዎች ከሰብሳቢው ጋር በመነጋገር ያዘጋጃል፣ ይህንኑ አጀንዳም ለሥራ አመራር ቦርድ አባላት ከስብሰባው 3 ቀናት በፊት እንዲደርስ ያደርጋል፤

2/ የቦርዱን ስብሰባ አጀንዳዎች ከሰብሳቢው ጋር በመነጋገር ያዘጋጃል፣ ይህንኑ አጀንዳም ለሥራ አመራር ቦርድ አባላት ከስብሰባው 3 ቀናት በፊት እንዲደርስ ያደርጋል፤

3/ የስራ አመራር ቦርዱ የሚያደርገውን ስብሰባ ቃለጉባኤ መዝግቦ ይይዛል፣ የስብሰባውን ሰነድም በቦርዱ አባላት ፊርማ እንዲፀድቅ እና በሰነድነትም እንዲያዝ ያደርጋል፤

4/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በአደራጁ አካል መረጃና ማብራሪያ ሲጠየቅ መልስ ይሰጣል፡፡

## 25. የስራ አመራር ቦርድ ስብሰባ

1/ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በሚወስነው መሠረት የሥራ አመራር ቦርዱ መደበኛ ስብሰባውን ያደርጋል፣ እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤

2/ ስብሰባው ምልዐተ ጉባኤ የተሟላ የሚሆነው ከስራ አመራር ቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሆኑ ሲገኙ ብቻ ይሆናል፤

3/ የስብሰባው ውሳኔ በድምፅ ብልጫ የሚወሰን ሆኖ እኩል ድምፅ ከመጣም ሰብሳቢው የደገፈው ሃሳብ ይፀድቃል፤

4/ ዝርዝር የአሰራር መመሪያ ቦርዱ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 26. የማህበሩ ዋና ስራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ቀጥታ ተጠሪነቱ ለማሕበሩ የሥራ አመራር ቦርድ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1/ የስራ አመራር ቦርድ ስብሰባዎች ላይ ያለ ድምጽ ይሳተፋል፤

2/ ከማህበሩ የሥራ አመራር ቦርድ በሚሰጠው የስራ መመሪያ መሰረት የማህበሩን ጽ/ቤት በማዋቀርና በሙያተኛ በማጠናከር ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

3/ ማህበሩ ለሚሰጠው አገልግሎት ከሚመለከታቸው ጋር የስራ ውሎችን ይዋዋላል፣ የመፃፃፍ ስራዎችን ያከናውናል፣ ማህበሩን ወክሎም ይከሳል ይከሰሳል፤

4/ ለማህበሩ የሥራ እንቅስቃሴ አስፈላጊ የሆኑትንና በስሩ ያሉትን የሥራ ክፍሎች ያዋቅራል፣ የሥራ ዕቅድና ማስፈፀሚያ በጀት አጥንቶ ያቀርባል፣ ለቦርዱም አቅርቦ ያፀድቃል፤

5/ በሚፈቀድለት የሥራ ማስፈፀሚያ በጀት መሠረት ለሥራው የሚያስፈልጉ የስራ አካላትና አወዳድሮ በመቅጠር ለሥራ አመራር ቦርዱ አቅርቦ ያፀድቃል፡፡ ለሥራ ክፍሎቹም ሠራተኞች የሥራ መመሪያና ዝርዝር የሥራ ድርሻ በማዘጋጀት ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

6/ ለማሕበሩ ሥራ የሚያስፈልጉ ሠራተኞችን ቅጥርና ስንብት ያከናውናል፤

7/ ከሥራ አመራር ቦርዱ በሚሰጠው የስልጣን ውክልና መሰረት ከአመራር ቦርዱ ከሚወከሉ አባላት ጋር በሆን የማሕበሩን ቼክ ይፈርማል፣ የወጪ ክፍያዎችን ይፈቅዳል፣ ያፀድቃል፤

8/ ለማህበሩና ለቦርዱ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች ያስፈፅማል፤

9/ የማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል፡፡

# ክፍል ስምንት

# የህዝብትራንስፖርት ማህበራት ሰራተኞችእናየማህበሩ አባላቶች ላይ የዲስፕሊን እርምጃ የሚያስወስዱ ጥፋቶች

## 27. የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት ሰራተኞች

1/ የአባላት ተሽከርካሪዎች የሚገለገሉበት ትኬት፣ ደረሰኝ እና ታግእንዲያዘጋጁ አለማድረግ

2/ ከቢሮዉ ፍቃድ ሳይሰጥ ከማህበሩ አባላት ዉጭ ለሆኑ ተሽከርካሪዎች ትኬት፣ ደረሰኝ እና ታግ መስጠት፤

3/ የማህበሩ አባላት ለሆኑ ተሽከርካሪዎች ለሚሰሩ ሰራተኞች ሰራተኝነታቸውን ሊያረጋግጥ የሚችል በፎቶ ግራፍ ተደገፈ መታወቂያ እንዲያዘጋጅ አለማድረግ፤

4/ የማህበሩ አባላት በሆኑ ተሽከርካሪዎች ለሚሰሩ ሰራተኞች ሰራተኝነታቸውን ሊያረጋግጥ የሚችል የደንብ ልብስ እንዲያዘጋጁ አለማድረግ፤

5/ ለማህበሩ ተሽከርካሪዎች የማህበሩ አርማ አለማዘጋጀትና እንዲለጥፉ አለማድረግ፤

6/ ቢሮዉ እንዲላክለት የሚጠይቃቸዉን መረጃዎችና ሪፖርቶች በወቅቱ አለመላክ፤

7/ የማህበር አባል ለመሆን መመዘኛውን የሚያሟሉ ኦፕሬተሮች በአባልነት ተቀብሎ አለማስተናገድ፤

8/ አባሉ መልቀቂያ እንዲሰጠዉ ሲጠይቅ መልቀቂያ አለመስጠት፤

9/ ከሌላ ማህበር ለቆ መምጣቱን በቂ መረጃ እያለዉክሊራንስ ሳይጠየቅበአባልነት መመዝገብ፤

10/ መመሪያው /መተዳደሪያ ደንቡ/ ከሚፈቀደው በላይ የማህበር አመራር አካላት የቆይታ ጊዜ ማራዘም፤

11/ ከስራ አመራር ቦርድ ዉሳኔ ዉጪ የማህበሩን ገንዘብ ስራ ላይ መዋል፤

12/ በማህበሩ ዉስጥ በአባልነት የተመዘገበ የተሽከርካሪ ባለንብረትን ቅጥር ሰራተኛማድረግ፡፡

## 28.የማህበር አባል በተመለከተ

የስራ አመራር ቦርድ የሚወስነዉን ልዩ ልዩ ክፍያ አለመክፈል፡፡

## 29. ስለቅጣት

የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብቶች ማህበር አባላትና ቅጥር ሰራተኞች በዚህ መመሪያ የተገለጹትን የስነምግባር ወይም የስነ-ስርአት ጉድለቶች በሚፈጽሙበት ወቅት የዲሲፒሊን እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ይደረጋል፡ በዚህም መሰረት የሚወሰድባቸዉ የዲሲፒሊን እርምጃ እና የቅጣቱ መጠን በዚህ አንቀጽ ከዚህ ቀጥሎ በሰፈረዉ ሰንጠረዥ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ | የስነምግባር ወይም የስነ-ስርአት ጉድለቶች | የቅጣት ደረጃዎች | | | እርምጃ የሚወሰድበት አካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | | |
| 1 | የአባልነት ተሸከርካሪዎች የሚገለገሉበት ትኬት፣ ደረሰኝ እና ታግ አለማዘጋጀት | 500 | 1000 | 1500 | ስራ አስኪያጅ | ጥፋቱ ለ4ኛ ጊዜ ከተፈጸመ ማህበሩ የሰራተኛዉን ቅጥር ይሰረዛል |
| 2 | ከቢሮዉ ፈቃድ ሳይሰጠዉ ከማህበሩ አባላት ዉጭ ለሆኑ ተሸከርካሪዎች ትኬት፣ ደረሰኝ እና ታግ መስጠት | 1000 | | | ስራ አስኪያጅ/ስምሪት ሰራተኛ | ጥፋቱ ለ2ኛ ጊዜ ከተፈጸመ ማህበሩ የሰራተኛዉን ቅጥር ይሰረዛል |
| 3 | የማህበሩ አባላት በሆኑ ተሸከርካሪዎች ለሚሰሩ ሰራተኞች ሰራተኝነታቸውን ሊያረጋግጥ የሚችል የደንብ ልብስ እንዲያዘጋጅ አለማድረግ | 250 | 500 | 750 | ስራ አስኪያጅ | ጥፋቱ ለ4ኛ ጊዜ ከተፈጸመ ማህበሩ የሰራተኛዉን ቅጥር ይሰረዛል |
| 4 | የማህበሩ አባላት ለሆኑ ተሸከርካሪዎች ውስጥ ለሚሰሩ ሰራተኞች ሰራተኝነታቸውን ሊያረጋግጥ የሚችል በፎቶ ግራፍ በተደገፈ መታወቂያ እንዲያዘጋጅ አለማድረግ | 250 | 500 | 750 | ስራ አስኪያጅ | ጥፋቱ ለ4ኛ ጊዜ ከተፈጸመ ማህበሩ የሰራተኛዉን ቅጥር ይሰረዛል |
| 5 | በማህበሩ ተሸከርካሪዎች ላይ የሚለጠፍ የማህበሩን አርማ አለማሳተም | 250 | 500 | 750 | ስራ አስኪያጅ | ጥፋቱ ለ4ኛ ጊዜ ከተፈጸመ ማህበሩ የሰራተኛዉን ቅጥር ይሰረዛል |
| 6 | ቢሮዉ እንዲላክለት | 500 | 100 | 1500 | ስራ | ጥፋቱ ለ4ኛ ጊዜ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የሚጠይቃቸዉን መረጃዎችና ሪፖርቶች በወቅቱ አለመስጠት | | 0 | | አስኪያጅ/ስምሪት ሰራተኛ | ከተፈጸመ ማህበሩ የሰራተኛዉን ቅጥር ይሰረዛል |
| 7 | አባላት መልቀቂያ እንዲሰጣቸዉ ሲጠይቁ መልቀቂያ አለመስጠት፤ | 500 | 1000 | 1500 | ስራ አስኪያጅ | ጥፋቱ ለ4ኛ ጊዜ ከተፈጸመ ማህበሩ የሰራተኛዉን ቅጥር ይሰረዛል |
| 8 | መመሪያ በሚፈቀደው መሰረት የአባልነት ጥያቄ አለመቀበል | 500 | 1000 | 1500 | ስራ አስኪያጅ | ጥፋቱ ለ4ኛ ጊዜ ከተፈጸመ ማህበሩ የሰራተኛዉን ቅጥር ይሰረዛል |
| 9 | ከሌላ ማህበር ለቆ መምጣቱን በቂ መረጃ እያለዉ ክሊራንስ ሳይጠየቅ በአባልነት መመዝገብ | 1000 | 2000 | 3000 | ስራ አስኪያጅ | ጥፋቱ ለ3ኛ ጊዜ ከተፈጸመ ማህበሩ የሰራተኛዉን ቅጥር ይሰረዛል |
| 10 | መመሪያው /መተዳደሪያ ደንቡ/ ከሚፈቀደው በላይ የማህበር አመራር አካላት የቆይታ ጊዜ ማራዘም | 1000 | | | ስራ አመራር ቦርድ | ጥፋቱ ለ2ኛ ጊዜ ከተፈጸመ የማህበሩ ፈቃድ ይሰረዛል |
| 11 | ከስራ አመራር ቦርድ ዉሳኔ ዉጪ የማህበሩን ገንዘብ ማባከን | | | | ስራ አስኪያጅ | ቅጥሩ ተሰርዞ በህግ ይጠየቃል |
| 12 | በቁጥጥር ወቅት የሰዉ ሃልና የቢሮ አደረጃጀት አንድሎ መገኘት | 500 | 1000 | | ስራ አስኪያጅ | ጥፋቱ ለ3ኛ ጊዜ ከተፈጸመ ማህበሩ የሰራተኛዉን ቅጥር ይሰረዛል |
| 13 | በማህበሩ ዉስጥ በአባልነት | 500 | 100 | | ስራ አስኪያጅ | ጥፋቱ ለ3ኛ ጊዜ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተመዘገበ የተሽከርካሪ ባለንብረት በቅጥር ሰራተኛነትመመደብ | | 0 | | | ከተፈጸመ ማህበሩ የሰራተኛዉን ቅጥር ይሰረዛል |
| 14 | በጠቅላላ ጉባኤዉ የተወሰኑ ልዩ ልዩ ክፍያዎችን አለመክፈል | 500 | 100<br>0 | 1500 | ኦፕሬተሩ | ጥፋቱ ለ4ኛ ጊዜ ከተፈጸመ የተሰጠዉ ፈቃድ ይሰረዛል |

## ክፍል ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 30. ልዩ ሁኔታ

1/ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት ፈቃድ የሚሰጡ እና የሚያድሱ ቢሮዉ እና የዞን መንገድና ትራንስፖርት መመሪያዎች ናቸዉ፤

2/ ከላይ በአንቀጽ 30(1) የተገለጸዉ ቢኖርም ቢሮዉ አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘዉ ሜትሮፖሊታንት እና መካከለኛ ከተሞች ፈቃድ እንዲሰጡ እና እድሳት እንዲያደርጉ ሊፈቅድ ይችላል፤

3/ ማህበር ለመመስረት የሚያስችል ሁኔታ በማይኖርበት ጊዜ / ማለትም ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ ሶስት የአባላት ቁጥር ከ 50 በታች ልዩ ደግሞ ከ15 በታች ከሆነ/ ማህበር ለመመስረት ቁጥራቸዉ እስከሚሞላ ድረስ ለአደራጁ አካል በማሳወቅ በመረጡት ማህበር ተጠግተዉ ለማህበሩ ኮሚሽን እየከፈሉ ስምሪት እንዲሰጡ መደረግ አለበት፡፡ አደራጁ አካል ቁጥራቸዉ 50 ከሆነ አዲስ ማህበር እንዲያቋቁሙ ማድረግ አለበት፤

4/ ተቀጣሪ ሰራተኞች በተቀጠሩበት ማህበር አባል የሆነ ተሽከርካሪ ሊኖራቸዉ አይገባም፤

5/ በስራ አመራርነት እያገለገለ ያለ የስራ አመራር አባል ተሽከርካሪዉን ሲሸጥ፣የተሽከርካሪዉ ደረጃ ሲወርድ ወይም ከፍ ሲል እና አመራሩ በተለያዩ ምክንያት ከማህበሩ ሲለቅ ወዲያዉኑ ከስራ አመራር ቦርድ አባልነት መነሳት/ መልቀቅ/ አለበት ይህንኑም ለአደራጁ አካል መሳወቅ አለበት፤

6/ አንድ የማህበር ከማህበሩ እዉቅና ዉጪ ያለበቂ ምክንያት ለተከታታይ 10 ቀናት የስምሪት አገልግሎት መስጠት ካቋረጠ ከማህበር አባልነት ይሰረዛል ነገር ግን ስምሪት መስጠት ያልቻለዉ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር መሆኑን ማስረጃ ካቀረበና ማስረጃዉ በአደራጁ አካል ተቀባይነት ካገኘ ሳይቀጣ በማህበሩ እንዲቀጥል ይደረጋል ያቀረበዉ ማስረጃ በአደራጁ አካል ተቀባይነት ካላገኘ ተሽከርካሪዉ ስምሪት መስጠት ከቋረጠበት ቀን ጀምሮ ለእያንዳንዱ 15 ቀናት ብር 600 ተቀጥቶ ወደ አባልነት እንዲመለስ ይደረጋል፤

7/ አንድ የማህበር አባል የማህበር አባል ሆኖ ለመቀጠል የሚያስችሉ መስፈርቶች ማለትም /አመታዊ ቦሎ፣ ኦፕሬተር ፈቃድ፣ የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ/ ማሟላት ሳይችል ከማህበር አባልነት ይሰረዛል ነገር ግን ከማህበር ለመሰረዝ ያበቃዉ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ማስረጃ ካቀረበና ማስረጃዉ በአደራጁ አካል ተቀባይነት ካገኘ ሳይቀጣ በማህበሩ እንዲቀጥል ይደረጋል ያቀረበዉ ማስረጃ በአደራጁ አካል ተቀባይነት ካላገኘ አባሉ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ለእያንዳንዱ 15 ቀናት ብር 400 ተቀጥቶ ወደ ነበረበት ማህበር ይመለሳል፤

8/ በመመሪያ ቁጥር 6/2004 ዓ.ም መሰረት የተቀጠሩ እና የስራ መደቡ የሚጠይቀዉን የትምህርት ደረጃ ማለትም ድግሪ ወይም ዲፕሎማ አሟልተዉ ነገር ግን የትምህርት አይነት/መስክቸዉ/ ተመሳሳይነት ባይኖረዉም በማህበሩ እንዲቀጥሉ ይደረጋል፤

9/ በመመሪያ ቁጥር 6/2004 ዓ.ም መሰረት ዲፕሎማ ኖራቸዉ በስራ አስኪያጅ የስራ መደብ የተመደቡ ሰዎች ከስራ መደቡ ተያያዠናት ያለዉ 4 አመት እና ከዚያ በላይ የስራ ልምድ ያላቸዉ በማህበሩ እንዲቀጥሉ ይደረጋል፤

10/ በመመሪያ ቁጥር 6/2004 ዓ.ም መሰረት 10ኛ/12ኛ ክፍል አጠናቀዉ በዋነዉ ጽ/ቤትም ሆነ ቅ/ጽ/ቤት በኦፕሬሽን/ በስምሪት ባለሙያነት፣ በመረጃና የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ፈጠራ ባለሙያ እና በሂሳብ ባለሙያነት የተመደቡ ሰዎች ከስራ መደቡ ተያያዥናት ያለዉ 4 አመት እና ከዚያ በላይ የስራ ልምድ ያለቸዉ በማህበሩ እንዲቀጥሉ ይደረጋል፤

11/ ከላይ በአንቀጽ 30(8)-(10) የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በተለያዩ ምክንያቶች የስራ መደቦች ሲለቀቁ ወይም ለአዲስ ማህበር ፈቃድ ሲሰጥ በአዲሱ መመሪያ እና በማሻሻያዉ የተገለጸዉን ተፈላጊ የትምህርት ዝግጅት የሚያሟሉ ሰዎች ብቻ እንዲመደቡ መደረግ አለበት፤

12/ ማህበሩ የፈረሰዉ ማህበሩን ሊያሰረዝ የሚያስችል ጥፋት ፈጽሞ ከመገኘት ጋር በተገናኘ ከሆነና በፈረሰዉ ማህበር የነበሩ አባላቶች ሌላ ማህበር የሚያቋቁሙ ከሆነ በፈረሰዉ ማህበርበቦርድ አባልነት ተመርጠዉ ይሰሩ የነበሩአባላት በአዲስ በሚቋቋመዉ ማህበር አባል ከመሆን ባለፈ ቢያንስ ለሁለት ምርጫ ዘመን በአመራርነት መመረጥ አይችሉም፡፡

## 31. ቅሬታ ስለማቅረብ

1/ በዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያ ደረጃ

ሀ) በተሰጠው የዲሲፕሊን ቅጣት ውሳኔቅርየተሰኘ ሰራተኛ ወይም የማህበር አባል ጉዳዩን የሚመለከተው አካል ውሳኔ በሰጠ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ የቅሬታ ማመልከቻውን በጽሁፍ አዘጋጅቶ ለመምሪያው አገልግሎት አሰጣጥ ማስተግበሪያ፣ ቅሬታና አቤቱታ ማስተናገጃ ክፍል ሊያቀርብ ይችላል፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አቤቱታ የቀረበለት አካል ጉዳዩ በቀረበለት 3 የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት አለበት፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2) በተሰጠ ውሳኔ ያልተስማማ አቤቱታ አቅራቢ ውሳኔ በተሰጠ 2 ቀናት ውስጥ ለመምሪያ ኃላፊ አቤቱታውን ያቀርባል፤ ኃላፊውም በሁለት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፤

መ) በመምሪያ ኃላፊው ውሳኔ ያልተስማማ ሰራተኛ ወይም የማህበር አባል ለቢሮው አገልግሎትና ቅሬታ ማስተናገጃ ዳይሬክቶሬት ሊያቀርብ ይችላል፤ በዚህም ካልረካ ለቢሮ ሃላፊው አቅርቦ ኃላፊው በ2 ቀናት ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

ሠ) በቢሮ ኃላፊው በተሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ አቤቱታ አቅራቢ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ማቅረብ ይችላል።

2/ በቢሮ ደረጃ

ሀ) በተሰጠው የዲሲፕሊን ቅጣት ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰራተኛ ወይም የማህበር አባል ጉዳዩን የሚመለከተው አካል ውሳኔ በሰጠ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ የቅሬታ ማመልከቻውን በጽሁፍ አዘጋጅቶ ለቢሮዉ አገልግሎት አሰጣጥ ማስተግበሪያ፣ ቅሬታና አቤቱታ ማስተናገጃ ክፍል ሊያቀርብ ይችላል፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አቤቱታ የቀረበለት አካል ጉዳዩ በቀረበለት 3 የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት አለበት፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2) በተሰጠ ውሳኔ ያልተስማማ አቤቱታ አቅራቢ ውሳኔ በተሰጠ 2 ቀናት ውስጥ ለቢሮ ኃለፊ አቤቱታውን ያቀርባል፤ ኃላፊውም በሁለት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፤

መ) በቢሮ ኃላፊው በተሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ አቤቱታ አቅራቢ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ማቅረብ ይችላል።

## 32. የእርምጃ አወሳሰድና አፈጻጸም

1/ በዚህ መመሪያ የተገለጹትን የስነምግባር ወይም የስነ-ስርአት ጉድለቶች የማህበሩ ሰራተኞ በሚፈጽምበት ወቅት አደራጁ አካል በማህበሩ ጥፋት የፈጸመዉን ሰራተኛ እርምጃ እንዲወስድበት ያሳዉቃል፤ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ በሰራተኛዉ ላይ የወሰደዉን እርምጃ እና ቅጣቱ ከሰራተኛዉ ከደሞዙ ተቆርጦ ለመንግስት ገቢ ማድረጉን ለአደራጁ አካል ያሳዉቃል ስራ አስኪያጁ ይህንን ማስፈጸም ካልቻለ እራሱ ሃላፊነት ይወስዳል/የቅጣቱን ገንዘብ እራሱ ይከፍላል፤

2/ በዚህ መመሪያ ከላይ በአንቀጽ 32(1) የተገለጸዉ ቢኖርም ይህንን ቅጣት ለመፈጸም ፈቃደኛ ያልሆኑ የቅጥር ሰራተኞችና ሌላ ለመባረር የሚያበቃ ጥፋት መፈጸማቸዉ ሲረጋገጥ

ሀ) የስራ አስኪያጅ በስራ አመራር ቦርድ

ለ) የሌሎች ሰራተኞችን በስራ አስኪያጅ የማባረር ዉሳኔ ይሰጣል

3/ በዚህ መመሪያ የተገለጹትን የስነምግባር ወይም የስነ-ስርአት ጉድለቶች የማህበሩ አባላት በሚፈጽሙበት ወቅት የቅጣት ዉሰኔ እንዲተላለፍባቸዉመረጃዉን ለቢሮ ማቅረብ ይኖርበታል፤

4/ ከህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት አደረጃጀት አኳያ በዚህ መመሪያ ያልተካተቱ ቅጣቶች በፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን መጋቢት 2005 ባወጣዉ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት አደረጃጀት ብቃት ማረጋገጫና ሥምሪት የሥራ ሂደት የአፈጻጸም መመሪያየተካተቱ ከሆነ የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ተግባራዊ መደረግ አለበት፤

5/ የቅጣቱ ሪከርድ የሚያገለግለዉ ለበጀት አመቱ ብቻይሆናል፡፡

## 33. የመተባበር ግዴታና የወንጀል ሀላፊነት

1/ ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ ለማስፈጸም ስልጣን ከተሰጣቸው አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፤

2/ ይህን መመሪያ የጣሰ ወይም ያሰናከለ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10.3 ሥር በተደነገገው ሠንጠረዥ መሰረት ተጠያቂ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በህዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ላይ በሚፈጽማቸው ሌሎች ወንጀሎች አግባብ ባለው ህግ ከመጠየቅ አይድንም፡፡

## 34. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

1/ ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም ሌላ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ-በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፤

2/ ከዚህ ቀደም በቢሮዉ ተዘጋጅተዉ የተላኩየሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር የአገልግሎትአሰጣጥ እና የአሰራር መመሪያ ቁጥር 6/2004 ዓ.ም እናየ2005 ዓ.ም የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር የአደረጃጀትና የአሰራርመመሪያ ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡

## 35. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ ማሻሻያ መድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 36. መመሪያው ስራ ላይ ስለሚውልበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ከፀደቀበት ከ21/10/2011 ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም ይህ መመሪያ በፍትሕ ቢሮ ከተመዘገበበትና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኃላ ተፈጻሚነት የሚኖረው በአማራ ክልል መንገድ፣ ትራንስፖርትና ሎጀስቲክ ቢሮ ድረ ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡